**መግቢያ**
የሲያትል ከተማ የ2023/2024 የሜዳልያ እድሳት ወቅት በኤፕሪል 1፣ 2023 ጀምሮ በጁን 30፣ 2023 ይጠናቀቃል። በጁላይ 15፣ 2023 የዘገየ ክፍያ (ሌት ፊ) ከመጀመሩ በፊት የሁለት-ሳምንታት ያለመቀጫ ክፍያ የሚከፈልበት ጊዜ ይኖራል። ባለፉት አመታት ስናደርገው እንደነበረ ማህበሮች እና ድርጅቶች የሜዳልያ እድሳት በተመለከተ በስፋት መረጃ እንዲያጋሩ እየጠየቅን ነው።

**የሲያትል የንግድ ፈቃድ ግብር ምስክር ወረቀትዎን (ሲያትል ቢዝነስ ላይሰንስ ታክስ ሰርቲፊኬት) ያረጋግጡ (ወይም ያውጡ)**
የሜዳልያ እድሳት ከመጀመርዎ በፊት አመልካቾች፣ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት ወይ ለማሳደስ፣ ወይም ተያያዥ የግብር ቅጾች ፋይል ለመድረግ **የከተማው የንግድ ፈቃድ ግብር ምስክር ወረቀት ድረገጽ** እንዲጎበኙ አጥብቀን እናበረታታለን። ይህንን ደረጃ ማጠናቀቅ የሜዳልያ እድሳት ሂደትን የበለጠ ቀላል ለማድረግ ይረዳል።

**ሜዳሊያዎን ያድሱ**

| | |
|---|---|
| በኦንላይን ያድሱ | • የሌለዎት ከሆነ **የሲያትል አገልግሎቶች ፖርታል** ሂሳብ (**ሲያትል ሰርቪስስ ፖርታል** አካውንት) ይክፈቱ።<br>• እድሳቱን ለማጠናቀቅ የፖርታሉ በራስ-አገልግሎት (ሰልፍ-ሰርቪስ) አማራጭ ይጠቀሙ።<br>• ክሬዲት ካርድ በመጠቀም በኦንላይን ይክፈሉ - ስልክ መደወል ወይም ወደ ቢሮ መምጣት አያስፈልግም! |
| ኢ-መይል በመጠቀም ድጋፍ ይጠይቁ | • የመኪና ምዝገባ ሰነድዎን (ቭሂክል ረጂስትሬሽን) ፎቶ ወደ **taxicab@seattle.gov** ይላኩ።<br>• ከሜዳልያው ጋር የተያያዘችው መኪና ባለፉት 12 ወራት ውስጥ **የከተማ መስተዳደሩ ፈቃድ በሰጠው መካኒክ** የደህንነት ምርመራ (ኢንስፔክሽን) ማለፍዋን ያረጋግጡ።<br>• የመድህን ደላላዎ (ኢንሹራንስ ብሮከር) የእርስዎን በስራ ላይ ያለ የመድህን ፖሊሲዎ/ማያያዣ (አክቲቭ ኢንሹራንስ ፖሊሲ/ባይንደር) ወደ **vehicleinsurance@seattle.gov** መላኩን እርግጠኛ ይሁኑ። |
| በአውደ ጥናት ይሳተፉ | • ከመይ-ኦጋማሽ ጀምሮ የሜዳልያ ባለቤቶችን በኦንላይን በማሳደሱ ረገድ ድጋፍ ለመስጠት የከተማው ተወካዮች አውደ ጥናቶች ያካሂዳሉ። **የአውደ ጥናት ቦታዎች በቀጠሮ ብቻ ነው የሚሞሉት።**<br>• የሚፈልጉት ቦታና ቀን ቀጠሮ በኦንላይን መደረግ ይችላሉ። የቀጠሮ መረጃ የያዘ ማረጋገጫ ኢ-መይል ይቀበላሉ። |

**ሌሎች ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው አስፈላጊ ነገሮች**

## በድጋሜ የተገነቡ የባለቤትነት ደብተሮች (ሪቢዩልት ታይትልስ) ያላቸው ተሽከርካሪዎች

በታክሲ ወይም በኪራይ (ፎር-ሀየር) አገልግሎት ያልነበረች በድጋሚ የተገነባ የባለቤትነት ደብተር (ሪቢዩልት ታይትል) ያላት ተሽከርካሪ እየጨመሩ ከሆነ፣ **የከተማ መስተዳደሩ ፈቃድ በሰጠው መካኒክ** ያጠናቀቀው የፍሬምና ኤየርባግ ምርመራ (ኢንስፔክሽን ማድረግ ይኖርብዎታል።

## የተሽከርካሪ ዕድሜ ገደብ

ከተማውና ካውንቲው ለታክሲና ለኪራይ (ፎር-ሃየር) ተሽከርካሪዎች የሚሆን አዲስ 15-ዓመት የተሽከርካሪ የእድሜ ገደብ የህግ ሃሳብ አቅርበው ተግባራዊ እስኪያደርጉት ድረስ ግዜያዊ እገዳ ተደርጎበት የቆየው የ10 ዓመት የተሽከርካሪ እድሜ ገደብ በቦታው እንደተጠበቀ ይቆያል። ከተማውና ካውንቲው ከዲሰምበር 31፣ 2023 በፊት አዲስ የእድሜ ገደብ በቦታውይኖራል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ።

## የታክሲሜትር ሙከራዎች (ታክሲሜትር ቴስትስ)

ተሽከርካሪዎች ወይም ማህበሮች ለሚቀይሩ የታክሲሚተር ሙከራዎች በ805 S. Dearborn St. Seattle, WA 98134 በሚገኝ ቢሮዎቻችን ለመጎብኘት ቀጠሮ ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል። ቀጠሮው የሚያዘው የሜዳልያ እድሳት በሚደረግበት ጊዜ ይሆናል።

## የባለቤትነት ዝውውሮች

በእድሳት ጊዜ የሚከናወኑ የባለቤትነት ዝውውሮች **በፈቃደኝነት የሚደረግ የሜዳልያ ዝውውር ቅጽ** ተሞልቶ ወደ taxicab@seattle.gov ኢሜይል መደረግ ይኖርበታል። ዝውውሮቹ በሲያትል አገልግሎቶች ፖርታል መደረግ አይችሉም። ዝውውሩ የሜዳልያ እድሳት በሚደረግበት ጊዜ ከተደረገ የሚከፈል ክፍያ አይኖርም።

## ዲርቦርን

**የሜዳልያ እድሳት እርዳታ በ 805 S Dearborn St. አድራሻ አይኖርም።** እርዳታ ለማግኘት የቁጥጥር ፈቃድ ሰጪ (ሬጉላቶሪ ላይሰንሲንግ) ተወካይን በስልክ ቁጥር (206-386-1268) ማነጋገር ይችላሉ፣ ወይም በኢሜይል አድራሻ (taxicab@seattle.gov) ማግኘት ይችላሉ ወይም በሚቀጥለው የሜዳልያ እድሳት አውደ ጥናት ቀጠሮ ማስያዝ ይችላሉ።

## መረጃ ለማግኘት ከታች ያሉትን ኪው.አር. ኮዶች (QR Codes) ይጠቀሙ

| | |
|---|---|
| 1. **የሲያትል ንግድ ፈቃድ የግብር ምስክር ወረቀት** | 2. **የደምበኛ አገልግሎት እና የአውደ ጥናት ቀጠሮዎች (ቡኪንግስ)** |
| 3. **የሲያትል አገልግሎቶች ፖርታል (ሲያትል ሰርቪስስ ፖርታል)** | 4. **በፈቃደኝነት የሚደረግ የሜዳልያ ዝውውር ቅጽ** |
| 5. **የተሽከርካሪ ምርመራ (ኢንስፔክሽን) ለማድረግ የከተማ መስተዳደር የፈቀደላቸው መካኒኮች (ደህንነት (ሴፍቲ)፣ ፍሬም፣ እና ኤርባግ)** | |